# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
# ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:- [illegible]ethionet.et


ቁጥር/Ref. No: መኢ/3/45/2003
ቀን/Date: 22/02/2003

**የተወደዳችሁ የሰማዕታት ቤተሰቦች፣**
**የተከበራችሁ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች፣**
**የተወደዳችሁ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ አባላትና ደጋፊዎች፣**

በየዓመቱ ጥቅምት 22 እና 23 በመንግሥታዊ ታጣቂ ኃይል የተገደሉትን ሰማዕታት ለማስታወስ በሚከበረው በዓል ዕለት በመካከላችሁ ተገኝቼ ንግግር እንዳደርግ ዕድል ስለተሰጠኝ ከፍተኛ ክብርና ደስታ ተሰምቶኛል፡፡

የዛሬ አምስት ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ የተዘረፈውን የምርጫ ድምጽ ለማስመለስ፣ በተለይም ሕገ-መንግሥታዊ መብቱ የሆነውን የመንግሥት ሥልጣን አመንጭነቱን፣ ባለቤትነቱንና ተቆጣጣሪነቱን ለማስከበር በአዲስ አበባ ከተማ እና በመላ ሀገራችን ሕዝባችን ሰኔ 1ቀን 1997 ዓ.ም እንዲሁም ጥቅምት 22 እና 23 1998 ዓ.ም በነቂስ ወጥቶ ባደረጋቸው ሰላማዊ ሰልፎች መንግሥታዊ ሥልጣኑ በሕዝብ ድምጽ ድርጅታችን ለነበረው ቅንጅት መሰጠቱን የተገነዘበው ኢህአዴግ ሕዝባችን የሀገሩን ዳር ድንበር እና ፀጥታውን እንዲያስከብርለት ባቋቋማቸው የገዛ ታጣቂ ኃይሎቹ የተጨፈጨፈበት፣ አካሉ የጐደለበት፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጐቿ በእየ በረሃው ታስረው ለወባ የተጋለጡበት እና የተሰቃዩበት፣ እንዲሁም ከሚወዷት ሀገራቸው እንዲሰደዱ የተደረጉበት ነበር፡፡

በማይቀረው ተፈጥሮአዊ ትዕዛዝ ከመካከላችን የተለዩን የመጀመሪያው የመኢአድ ፕሬዘዳንት ፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ እና መቶ አለቃ ወንድም ደፋር የመኢአድ የሰሜን ቀጣና ምክትል ኃላፊ እንዲሁም በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ያራምዱ በነበረው የሃሳብ ልዩነት ብቻ በኢህአዴግ ጥይት ለሕልፈት የተዳረጉት ጓዶቻችን ገና የመኢአድ ታጋይ ሆነው በጀመሩበት ማግሥት ለኢህአዴግ ማስፈራራት፣ እሥራት፣ ድብደባ እና ግድያ ሳይበገሩ፣ ባመኑበት በመኢአድ ሕዝባዊ ፕሮግራም ፀንተው ከሕዝብ ጐን በመቆም ታግለው በማታገላቸው ከ1997ቱና ከ1998ቱ ዓ.ም ሰማዕታቶቻችን ጋር እነኛን

የኢትዮጵያን ሕዝብ የቁርጥ ቀን ታጋዮች የምናስታውስበትም ቀን ነው የዛሬው የሰማዕታት ዕለት፡፡
ይህ ቀን ወጣቱ በኢህአዴጋዊ የጐሳ ፖለቲካ ተከፋፍሎ የጋራ ከሆነው ከትምህርቱና ከመማሪያ ተቋማዊ ነጻነቱ ማለትም ነጮች አካዳሚክ ፍሪደም ከሚሉት ይልቅ ጐሳውን እንዲያስብ የተደረገበትን ኢህአዴጋዊ ፖሊሲ የሚያወግዙበትም ነው፡፡

ከሁሉ በላይ ግን ይህ ቀን ሰላማዊ ትግል ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው እና እውነተኛ ሕዝባዊ ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍትሕ እና ዲሞክራሲ በሀገራችን ሰፍነው፣ መንግሥት ከጠመንጃ አፈሙዝ ሽግግር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተላቅቆ በዘላቂነት በሕዝብ ምርጫ ብቻ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚሸጋገርበት እና ሕዝባችን ከመንግሥት-ሠራሽ ረሀብና ድህነት የሚላቀቅበት መሳሪያ እንጂ የ1997ቱ እና የ1998ቱ ኢህአዴጋዊ የንፁሐን ወገኖቻችንን ሕልፈት ያየህ ተቀጣ ኢህአዴጋዊ ማስፈራሪያ እንዲቆም ሕዝባችን ጥያቄውን የሚያድስበትም ነው፡፡

ይህንን የሰማዕታት ቀን የአዲስ አበባ የመኢአድ ወጣት ምክር ቤት በያመቱ በእርሱ አዘጋጅነት እንዲከበር መኢአድን አስፈቅዶ እነሆ ዛሬ ሁላችንም ለሶስተኛ ጊዜ እንድንገናኝ ያደረገ በመሆኑ እንኳን ደስ አለን እንላለን፡፡

የአዲስ አበባ የመኢአድ ወጣት ም/ቤት ይህንን ብቻ አይደለም የወሰነው፡፡ በማናቸውም ሕብረተሰብ ወጣቱ የነጻነት ችቦ አቀጣጣይ ድርጅት ደግሞ የሕብረትና የኃይል ምንጭ መሆናቸውን ተገንዝቦ እስካሁን በኢህአዴጋዊ ፖሊሲ ተከፋፍሎ መቆየቱን በቁጭት በማስታወስ የመላ ኢትዮጵያ የመኢአድ ወጣት ም/ቤት በአስቸኳይ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲቋቋም እና ሕዝባዊ የመኢአድ ዓላማ እንዲያጐለብት ጥሪ ያቀረበ እና ይኸንኑ እውን ለማድረግ ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ መጀመሩን ያበሰረበት በመሆኑ የመኢአድ ማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ ከፍተኛ አክብሮት፣ አድናቆት እና ግምት የሚሰጠው መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

መኢአድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነትና ለብሔረሰቦቿ እኩልነት አያሌ መስዋዕትነት የከፈለ፣ እውነተኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕብረ-ብሔራዊ ፓርቲ መሆኑን በመገንዘብ ወጣቱ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና ከ80 ብሔረሰቦቿ ጐን በመሰለፍ የመኢአድን ፕሮግራም በማንገብ ሰላማዊ ትግሉን ለማጐልበት እና መኢአድን ከውስጥ አርበኞችና

አፈንጋጮች ለመጠበቅ ዳግመኛ ቆርጦ በመነሳቱ መኢአድ ደስተኛ መሆኑን እየገለጽን የቀድሞው የመኢአድ ወጣት ም/ቤት ጥቂት አባላት እና ሌሎችም በኢህአዴጋዊ መሠሪ ክፍፍል ተታልለው በሕብረ-ብሔራዊ እናት ድርጅታቸው መኢአድ ላይ ወንጀል በፈፀሙት እና አሁንም በመፈፀም ላይ ያሉት ተፀጽተው፣ ራሳቸውን በመውቀስ ከመላው ኢትዮጵያ ወጣት ጐን ተሰልፈው ዳግም በእናት ድርጅታቸው በመኢአድ ውስጥ የሚሰባሰቡበት እንዲፈጠር በሚያደርጉት ጥረት መላው የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ፣ አባላቱና ደጋፊዎቹ ሁሉ ከአዲስ አበባ የመኢአድ ወጣት ም/ቤት እንደማይለይ ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን፡፡

በዛሬው ዕለት መኢአድ የሰማዕታቱን ቤተሰቦች በዘላቂ የሕይወት የሥራ መስክ ለማደራጀት ማናቸውንም ጥረት ለማድረግ ዳግደኛ ቃል የምንገባበት መሆኑን ስናበስርላችሁ ከፍተኛ ደስታ እየተሰማን ነው፡፡

*የኢትዮጵያ ነጻነት እና አንድነት በትግላችን ይከበራል!*

*ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!*




ያዕቆብ ልኬ
የውጭ ጉዳይ ኃላፊ